STATE OF KANSAS
DEPARTMENT OF SOCIAL & REHABILITATION SERVICES
ECONOMIC & EMPLOYMENT SUPPORT

10-01-06

የሥራ ዝግጁነት ማጣሪያ

ቀን፡ _____ የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር፡ _____

ስም፡ _____ የትውልድ ዘመን፡ _____ ዕድሜ፡ _____

አድራሻ፡ _____ ስልክ #፡ _____

_____

የቅጥር ግቦች፡ _____

ባለፉት 12 ወራት የነበሩዎ ሥራዎች ብዛት፡ _____ ከፍተኛው ደሞዝ፡ _____

የመጨረሻውን ሥራዎን የለቀቁት ለምን ነበር? _____

በሥራዎ ያከናወኗቸው ተግባራት (በፊትም ሆነ አሁን) ምን ምን ናቸው?

_____

_____

አሁን እንዳይሠሩ ያገደዎት ምንድን ነው? _____

መሥራት የሚፈልጉት ምን ዓይነት ሥራ ነው? _____

የሚያሰጋዎ ጉልህ የጤና እክል ካለ ይጥቀሱ፡ _____

የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ወይም GED አለዎት? _____

በአሁኑ ወቅት ትምህርት ላይ ነዎት ወይስ ሥልጠና ላይ? _____

የኑሮ ሁኔታዎ የተረጋጋ ነው? _____

ከሙያ መልሶ ማቋቋሚያ (Vocational Rehabilitation) ወይም ከልጆችና ቤተሰብ አገልግሎቶች (Children and Family Services) ጋር ተባብረው እየሠሩ ነው? _____

ከHead Start ወይም Early Head Start ጋር ግንኙነት አለዎት? _____

የሚያሳስብዎ ማንኛውም ሕጋዊ ወይም የአሳዳጊነት ጉዳይ ካለ ይግለጹ፡ _____

አስተማማኝ መጓጓዣ ነው ብለው የሚጠቀሙት ምን እንደሆነ ይግለጹ፡ _____

ችግር ቢያጋጥምዎ በቅርብ ሊረዱዎ የሚችሉ ዘመድ ወዳጆች አሉዎት? _____

ልጆችዎን የሚጠብቅልዎ ማን ነው? _____

*እርስዎ ወይም ልጆችዎ ለአካላዊ፣ ስሜታዊ ወይም ወሲባዊ ጥቃት የተጋለጣችሁ ናችሁ? _____

*እርስዎ ወይም ልጆችዎ በሌላ ሰው ዛቻ ደርሶባችሁ ያውቃል? _____

ከአደንዛዥ ዕጽ ወይም ከአልኮል ጋር በተያያዘ ችግር አለብዎ? _____

በየዕለቱ የእርስዎን እንክብካቤ የሚፈልግ የአካል ጉዳተኛ ሰው አለ? _____

(*ከጀርባው ይመልከቱ)

* ቀጥሎ የቀረቡት ጥያቄዎች የTAF እገዛ ለማግኘት የሚያመለክቱ ሰዎችን ለመመዘን ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚመከሩ ናቸው (KEESM 1412.3 እና 2244ን ይመልከቱ)።

1. ልጆችዎ በእርስዎ ሕይወት ውስጥ ቦታ ባለው ግለሰብ ዛቻ፣ ጥቃት ወይም ጉዳት (ጉዳት ሲባል ማበሳጨትን ወይም እርስዎ፣ ልጆችዎ፣ የቤት እንስሳዎ ወይም ሌሎች ቤተሰቦች ወይም ወዳጆች ላይ ጉዳት ለማድረስ መዛትን፣ መግፋትን፣ ጭምቅ አድርጎ መያዝን፣ መጎሸምን፣ በጥፊ መምታትን፣ መምታትን፣ ማነቅን ወይም ወደ ታች መድፈቅን፤ ሁልጊዜ ማጣጣልንና የማይረቡ እንደሆኑ አድርጎ መናገርን፤ ማንኛውንም ዓይነት ያልተፈለገ ወሲባዊ ንክኪን ሊጨምር ይችላል) እየደረሰባቸው ነው?

2. በአሁኑ ወቅት ሥራ መሄድ፣ ሥራ መፈለግ፣ ወይም ወደ ትምህርት ቤት መሄድ እርስዎን ወይም ልጆችዎን ለአካላዊ፣ ስሜታዊ ወይም ወሲባዊ ጥቃት ሊያጋልጥ የሚችል በመሆኑ ምክንያት እገዛ ያስፈልግዎታል?

3. ቀደም ሲል በተፈጸመብዎ በደል ምክንያት (ለምሳሌ ያህል ፍርሃት፣ የመንፈስ ጭንቀት አለብዎ? ከቤት ወጥተው ወደ ሥራ ፍለጋ ወይም ወደ ትምህት ቤት ለመሄድ ወይም ለደረሰብዎ ጥቃት እርዳታ ለማግኘት ወደ ቴራፒስት ለመሄድ ይፈራሉ?) በአሁኑ ወቅት እገዛ ያስፈልግዎታል?

4. ከዚህ ቀደም እገዛ ያገኙ በነበረበት ጊዜ ጊዜዎን ያሳልፉ የነበረው በእርስዎ ወይም በልጆችዎ ላይ ዛቻ፣ ጥቃት ወይም ጉዳት የሚያደርሰውን ግለሰብ ለመቋቋም ወይም ከእርሱ ለማምለጥ (ለምሳሌ ያህል መጠለያ ውስጥ ነበሩ? ቤትዎን አጥተው ነበር? ሌላ ቦታ መቀየር ነበረብዎ? ወይም ሥራ ወይም ትምህርት ማቆም አስፈልጎዎ ነበር?) በመጣር ነበር?